# ፋኖ በል! ሞረሽ በል!
# ለአንተም ለሕዝብ
# ለእናት አገር ኢትዮጵያ
# ድል !

ከቀመሩ ደሳለኝ

በኢትዮጵያ የአማራው ኅብረተሰብ ሆነ ማንም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በኢትዮጵያ የግዛት አንድነት ውስጥ መንቀሳቀስ፣ መዘዋወር፣ መስራትና ሃብት ማፍራት፣ የተፈጥሮ የአገሪቱን ሃብት ሁሉ ተካፋይ ባለቤት ነው።

ማንም የባንዳ ልጆች፣ የማፊያ ወራሪ ጥርቅሞ በአምባገነን ሕገ-አልባነት አማራውን ሆነ ሌላውንም ሕዝቧን በክልል ሊወስን፣ በቋንቋ ሊገድብ፣ ሊያፈናቅልና ሊያባርር፣ ኢትዮጵያን በሕገ-ወጥ ሥርዓት ሊመራት ከቶ አይሆንም አይቻልም ። ኢትዮጵያ ምንጊዜም የኢትዮጵያኖች አገር እንጂ፣ እኛን የማይመስሉና የሚጠሉን፣ ሊያጠፉን የሚሞክሩ፣ አገርን የሚሸጡና ሃብትን የሚዘርፉ የባንዳ ወራሪዎች አይደለችም።

ወያኔ/ኢህአዴግ አምባገነን፣ ሕግ የማያውቅ ወራሪ ኃይል በጠበንጃ የሚያስተዳድር ገዥ እንጂ በሕግ የበላይነት የሚመራ ሕዝብን የሚወክል መሪና ፓርቲ አይደለም ። ይህ በሕግ የማይመራ ፋሽስት ተራ አምባገነን ኃይል ሕግን አይውቅም ፣ አያከብርም ተግባራዊነቱንም አይረዳም ።

የአንድ አገር ሕዝብ መንግሥትና ሕግ ኖሮት ሕግንም አክብሮ መኖር ሰላምና ደህንነት፣ የነፃነት መብትም ግደታም ነው ። ነገር ግን የወራሪን አምባገነን ፣ አገሪቱን አገሬ፣ሕዝቡንም እንደ ሕዝብ ወገኔ የማይል፣ በማክበር ፈንታ የሚያዋርድ፣ በመጠበቅ ፈንታ የሚበድልና የሚያጠፋውን ሕግ- ወጥ ሕግን ፣ የኃይል ሥርዓትን ተቀብሎ መኖር ነፃነት የጎደለው ፣ሰብዕና ያነሰው፣ መብት ያጣበት በመሆኑ ሕዝብ ይህን ዓይነት ሕግ እንደ ሕግ የበላይነት ተቀብሎ ሳይሆን መታገልና ማስወገድ፣ የነፃነት መብቱን፣ የአገሩን ክብርና ታሪክ እንዲፈራና እንዲታፈር፣ ሕዝብም እንዲታደግና እንዲኖር መጠበቅና ማስከበር የተፈጥሮ የሰው ልጆች የየትውልዱ ሁሉ የመኖር ባህሪና ግደታ ነው።

ወያኔ/ኢህአዴግ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ ከጅምሩ በጠላትነት ለማጥፋት፣ ለማንገላታት፣ ለማረዝ፣ ለማዳከም፣ አንድነትና ኅብረትን፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን፣ አረንጓዴ- ቢጫ-ቀይ ሰንደቅ ዓላማችንን በማናጋትና በማሳነስ አገርን በቋንቋ ክልል የከፈለና የእናት አገር ኢትዮጵያን አካል ሕገ-ወጥ ኃይልን ተጠቅሞ ያለሕዝቦች ፍላጎትና ፈቃድ ለሁለት የከፈለ፣ ሕገ-ወጥ ሕገ መንግሥትን የፈጠረ አምባገነን መንግሥት ነው። ይህ ሕግ-ወጥ ሕግም በወጣ ማግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ውድቅ የሆነ ተቀባይነት የሌለውና የተሻረ ሕግ መንግሥት በመሆኑ ተግባራዊነት የለውም ።

ወያኔ/ኢህአዴግ ፀረ-ሕዝብና ፀረ- አገር፣ የማፊያ ቡድን ወራሪ ጠላት ነው። ወያኔ የውሸትና የሃሰት ፕሮፓጋንዳ በመንዛት አጉል ዲሞክራሲ አመጣሁ፣ ለሁሉ እኩልነት ፈጠርኩ፣ እንደፈለጋችሁ ሁኑ እየተባለ አንዱን ክፍል ሕዝብ ወዳጁና መጠቀሚያው በማድረግ ሲሾምና ሲሸልም፣ ያገሪቱን ሃብት አብረው ሲዘርፉና ሲቀሙ በሌላ በኩል ደግሞ ሌላውን ክፍል ሕዝብ በተለይም የአማራውን ኅብረተሰብ ጠላቱና



EthioLion.Com

የማይጠቅም አድርጎ በመሰየም ሲያጣላና ሲያበጣብጥ፣ ሲያስርና ሲገድል፣ ሲያባርርና ሲያሳድድ፣ ጥላቻና የጥፋት በደልን ሲፈጽምና ሲያስፈጽም ይገኛል።

የተራ አምባገነኖች፣ የፋሽስት ባህሪና ሕገ-ወጥ የሃሰት ፕሮፓጋንዳ ፣የጥፋት ዲሞክራሲ ፣ የውሸት ተስፋ በወያኔ ዙሪያ ያሉትን አሽቃባጭ አናሳዎችና አድርባይ ሆዳሞች የአቶ መለስና ቡድኑ የክህደት ውሸትና ብልጣብልጥነት ግብዞችን ጊዜዊ ጥቅም ስለሰጣቸውና እጅግ ስለደለላቸው ወያኔ/ኢህአዲግን ተወዳጅ ጥሩ መሪና መንግሥት አስመስሎአቸውና መስሎአቸው በቀቢጠ-ተስፋ ሆኖላቸው ወደውትና አቅፈውት የተመሰገነም ጥሩ መንግሥት አስመስለው አገርና ሕዝብን እየሸጡና እያጠፉ በክህደት ስምሪታቸው ለ 21 ዓመታት ይገኛሉ። አገርና ሕዝብም በእጅጉ እየተጎዳና እየተሰቃየ ነው።ስለሆነም በዚህ ድርጊታቸው ሁሉም አብረው ይደመሰሳሉ።

የአማርው ሕዝብ በኢትዮጵያ የግዛት አንድነት የየብስ፣ የውሃና የአየር ክልል ሁሉ አገሩና መኖሪያ ቦታው ነው። አማራው የኢትዮጵያን አገራዊ ክልል ዳርድንበር ከፈጠሩትና ከወሰኑት ሕዝቦች መካከል አንዱና ዋናው ሉዕላዊነቷን፣ ሰንደቅ ዓላማዋን አረንጓዴ- ቢጫ-ቀይ ከፍ አድርጎ የሚያውለበልብ፣ ነፃነቷን ጠባቂና አስከባሪ፣ የታሪክና ኩራት ሁሉ ባለሙሉ መብት ባለቤት፣ ኃላፊነትና ግዴታም ያለው ንዋሪና መሰረታዊ ዜጋዋ በመሆኑ በፈለገውና በፈቀደው ቦታ ሁሉ ተዘዋውሮ የመኖር መብቱ ምንጊዜም ገደብ የለውም።

የሕወሓት ወራሪ አስተዳደር በማጂ ጉራ ፈርዳ የአማራውን አርሶ አደር ፣ ችግርን ፣ ረሃብን አሸንፈው መኖራቸውን፣ የወያኔን ሕግ-ወጥ ሕግ አክብረው መቀበላቸውና እያከፈሉ ላሉት ትዕግሥት ሁሉ አክብሮት ተነፍጎአቸው የዜግነት መብታቸው ተነፍጎ ከቦታና ከቤታቸው ሃብታቸውን እይተነጠቁ እንዲባረሩ ተደርጓል። ይህ ሁሉ እብሪት የአማራውን ተወላጅ ለማሰቃየትና ለማዳከም፣ ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት በአቀደውና በአለመው ሕገ-ወጥ ፀረ-ኢትዮጵያና ሕዝቧ ላይ ያለው የጥላቻ ተግባር ነው። ይህንም በድጋሜ የሚረጋግጥልን ዋናውና ከፍተኛው ማስረጃ ጠቅላይ ሚኒስተሩ አቶ መለስ ዜናዊ ሰብዕና የጎደለውና ደንታ ቢስ የአረመኔ ሥራና ተግባሩን ፓርላማዩ ለሚለው አቃባጪ መንጋዎች የክህደት ፕሮፓጋንዳውንና መሰሪ ሸፍጡን ሲገልጽ መሰማቱ ነው። ይህን ርካሽ ተግባሩን በቅድሚያ ያጋለጠውንና ተባረው ለተፈናቀሉት ወገኖች የመጠለያና የሚያስፈልግውን ርዳታ የሰጠውን የመኢአድ ፓርቲን እንደጥፋተኛ ለመወንጀል ሲያደባ ያሰማው ቃል ጭምር ነው።

ያም ሆነ ይህ ይህ ወርሪ መንግሥት ለኢትዮጵያና ኢትዮጵይዊነት የለየለት ጠላት ስለሆነ ኢትዮጵያዊ በተለይ የአማራው ኅብረተሰብ የወያኔን ትዕዛዝ ተቀብሎ ከቦታው መነሳትና መፈናቀል ፣ ተግባራዊ ማድረግ የለበትም።አሻፈረኝ ሊልና ሊአምጽ ይገባዋል ። ከአካባቢው ህዝብ ጋር በመግባባት ፣በመቻቻል፣ ተመሳስሎ በእኩልነትና በአንድነት አብሮ የሚሰራና የሚያርስ፣የሚኖር ፣ የሚበላውን ተካፍሎ የሚበላ፣ ተጋብቶና ተዋልዶ፣ተዛምዶም ኅብረተሰባዊ ትስስር ያለው ኢትዮጵያዊ ሕዝብ ነው ።

የማንኛውም አካባቢ ሕዝብ ሁሉ በኢትዮጵያዊነቱ ተባብሮና አንድ ሆኖ በአጋርነት ለምንንም ዓይነት ችግር አብሮ መቆምና መፋለም አለባቸው ። ሁሉም በአለበት ቦታ ጸንቶ በመኖር የጠላትን ሕገ-ወጥ ተጋባር በመቃወም አንዱ ወገን ሲበደልና ከቦታው ሲባረር፣ ሃብቱ ሲቀማ በዝምታና በትዕግሥት መቀበል የለበትም። በዝምታ ማየትና እየተላቀሱ መሸኘት ሳይሆን ተባብሮና ክንድን አጠንክሮ በቆራጥነት በጠላት ላይ መነሳትና አገርና ሕዝብን ማዳን ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የወቅቱ ተቀዳሚ ተግባር ነው።

EthioLion.Com

ኢትዮጵያ ለሁሉም ክፍል ሕዝቧ እኩልና ትክክል አንጡራ አገሩና ሃብቱ ናት። የጠላትን መጥፎ ሥራና ተግባር፣ የክህደትና የውሸት ፕሮፓጋንዳ ሁሉ ማጋለጥ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በየትኛውም ስፍራ ወያኔ እያደረሰ ያለውን የጭቆና ተግባር ሁሉ እያንዳንዱ ኢትትዮጵዊ እንድያውቀውና እንድተባበር እንድሁም ለአገርና ለወገን ተቆርቋሪ ፓርቲዎች፣ የሕዝብ ድርጅቶች፣ የአገርና የውጭ የመገናኛና ደኅረ-ገጾች፣ ሪፖርተሮች በቦታው እየተገኙ ሁኔታውንና የጥፋት ተግባሩን ማጋለጥና የወያኔ/ኢህአዴግ የግፍ ስራና ዘረፋ ሁሉ እንድመዘገብና እድያዝ መደረግ አለበት።

ይህን የወያኔ/ኢህአዴግ እብሪት ሕዝብ በአንድነት ሊከላከለው፣ ሊቋቋመው፣ ሊመክተው አገርንና ነፃነትን በኅብረት ለመጠበቅ ትውልዱን ማስተማርና ማደራጀት፣ መምራትና ኢትዮጵያዊ የሆነ መንግሥት መፍጠር፣ የሕዝብና የሕግ የበላይነት፣ ሕዝባዊ ዲሞክራስዊ ሥርዓት እንድፈጠርና ኢትዮጵያን መገንባት አስቸኳይና አንገብጋቢ የመፍትሄ ተግባራችን የአገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያልተቆጠበ ጥረት ነው።

በአገር ውስጥ ፣ በውጭ ዓለም በየትኛውም ቦታና ስፍራ ተሰዶና ተበትኖ የሚገኝ ኢትዮጵያዊ ሁሉ፥ በኢትዮጵያ የረዥም ሺህ ዓመታት ታሪክ በቀደምት አባቶችና እናቶች አጥንትና ደም ፣ መልካም ተግባር የተገነባች ኢትዮጵያ፣ የእኔም በትውልድና በታሪክ ኃላፊነት ግደታ አለብኝ፣ በኢትዮጵያዊነቴ የምኮራና የምመካ ለመጪው ትውልድ አገርና ታሪክን ማውረስ አለብኝ ብሎ በሕሌናው ራሱን የሚጠይቅና የሚያዘጋጅ ፣ የሚያምንና የሚያንጽ፥ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን፣ አረንጓዴ- ቢጫ- ቀይ ሰንደቅ ዓላማዋን የሚያስቀድም፣ የሕዝቧን አንድነት የሚያምንና የሚያደንቅ፣ የሚኮርበት ሁሉ በቆራጥነትና በፅናት አብሮ ተባብሮ መሰዋዕትነት ለመክፈል ሳያወላውልና ሳይዋዥቅ ወዳጅ ጠላትን ለይቶ በሰከነ ሁኔታ ለዚህ ቅዱሳዊ ኢትዮጵያዊነት ተግባር መደራጀት፣ ያለማወላወል ትዕዛዝ መቀበልና ተግባራዊ ማድረግ እምነቱና ፍላጎቱ ለሆነ ሁሉ አስቸኳይ የማይበገር አሸናፊና ድል አድራጊ ተግባር መፈጸም ዛሬ መሆን አለበት።

ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለአገር አንድነት፣ለሕዝብ መረጋጋትና ደህንነት፣ ሰላምና ብልጽግና የሚሻና የሚመኝ ሁሉ ፋኖ ሊል፣ ሞረሽ ሊል ጊዜው አሁን ነው። ማንም ከአገር ልጅ ከወንድሙና ከእህቱ፣ ከጎረቤትና ከአቅራቢያው ጋር ተባብሮ በድፍረትና በቆራጥነት ተነሳስቶ በአርበኝነት የሕዝብንና አገርን ሉዕላዊነት መጠበቅ የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ ብቻ ሳይሆን የማንኛውም የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የትውልድ ኃላፊነትና የታሪኩ ባለቤትነት ግደታ መሆን ይኖርበታል።

ስለዚህም ነው " አገር አትሞትም" ጠባቂ ትውልድ ሁልጊዜ አላት የሚባለው። ወጣቱ ትውልድ የሚጠበቅበትንና የተጣለበትን ታሪካዊ አደራ እውን ለማድረግ ወንድ ሆነ ሴት የተማረ ያልተማረው ፣ ነጋደ ገበሬው ፥ ወታደር አስተማሪው ቋንቋና ቦታ ሳይከልልና ሳይወስን ለመጪው ትውልድ ነፃና ብርቱ ኢትዮጵያን ማስረከብ የሚጠበቅ የዚህ ትውልድ የታሪክ ድርሻ ነው። ከዚህ ያነሰ በክህደትና በውሸት ፕሮፓጋንዳ ተላላ በመሆን መጭውን ትውልድ ለባርነትና በቋንቋ ክልል ተከፋፍላ የትዳከመች፣ ለም መሬቷ የትሸጠባት ኢትዮጵያን ማውረስ የማይጠብቅ ነው። ነፃነት የጎደለው ፣ የዜግነት መብትና ስበዕና ያነሰው፣ አገሩን ያስወረረ የኢትዮጵያዊ ባህሪ ፣ ወግም አይደለም። ኢትዮጵያዊነት ከምንም ከማንም በላይ የነፃነትና የዜግነት መብት ክብርና ኩርት ትልቅነትና መታፈሪያም ነው።

EthioLion.com

የአገር ስፋቱ፣ የሕዝብ ብዛቱ ዋናውና ቀዳሚ ሃብት በመሆኑ ይህን አውቆና ተረድቶ አገርና ሕዝብን ጠብቀንና ተንከባክበን ኢትዮጵያን ትልቅና የበለጸገች፣ የማትደፈርና የማትበገር አገር ማድረግ ጥንትም የነበረ ዛሬም ዘወትርም የሚኖር የየትውልዱ ሕልምና ፅኑ አገርዊ የሕዝብ ተግባር ነው።

ይህን ተግባራዊ ለማድረግ አስተባብሮና ጠብቆ ለመያዝ ሁሉም ፋኖ ሊል ፣ ሞረሽ ሊል ፣ ከአገር ልጅ ጋር በፅናት ሊቆም፣ ሊደራጅ፣ ሊዘምትና ሊታገል የያንዳንዱና የሁሉም የጋራ አስተዋጽዖ መስዋዕትነት መሆን አለበት።

እናት አገር ኢትዮጵያ ምንጊዜም ጠባቂ ትውልድ አላት !!

ፋኖ በል ! ሞረሽ በል !!

ለድል !!

ግንቦት 1/2004

EthioLion.Com